# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 5 ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.

# የ“ደም” ዕለት ፦ ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም.

*የ«ያ ትውልድ ተቋም»ን ድረ ገጽ ይፋ መደረግ 4ኛ ዓመት እና የሜይ ዴይ ሰማዕታትን ምክንያት በማድረግ*

በሀገራችን ሰኔና ሰኞ ይባላል። ከክርስትና አምነት አኳያ ስናያይዝ ዛሬ ሜይ ዴይ (ሚያዝያ 23) እና የፋሲካ በዓል፣ ስቅለትና ሚያዝያ 21 ገጥመዋል። ሌላው ገጠሞሽ የዛሬ 39 ዓመት ሚያዝያ 21 የዋለው ዓርብ ቀን ሲሆን ሜይ ዴይም ዕሁድ ነበር። የዛሬን ሚያዝያ 21 በጌታ እየሱስ ክርስቶስ ስቅለት የሚያስቡ ክርስቲያን ወገኖቻ የዛሬ 39 ዓመቱን ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በልጆቻቸው ጅምላ ጭፍጨፋ ያስቡታል። የሚያዝያ 23 ቀን ዕሁድ የፋሲካ ባህላቸው ደርግ በጅምላ የቀበራቸው ልጆቻቸው ሰልስት እንደነበር 39 ክረምትና በጋ ቆጥረው በሀዘን ያስቡታል። ጌታ እየሱስ ሞትን ድል አድርጎ በተነሳበት የፋሲካ በዓል በደርግ ጥይት በግፍ የተጨፈጨፉ ሕፃናትና ወጣቶችን ክብር ለእናንተ እያልን እናነሳቸዋለን። ዓጽማቸውን እንቀሰቅሳለን። እናከብራቸዋለን።

“እነሆ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” ብሎ ጌታችን ክርስቶስ ህይወቱን ለሰው ልጆች ኃጢአት ሰጠ። እንደ መጽሐፉ፤ የፈጠራቸው ልጆቹ ከመካድ አልፈው አሰቃይተው ሰቀሉት፣ ሰቅለው አላገጡበት። በእናቱ ቅድስት ማርያም ፊት አንድ ልጁን ሰቀሉት። ከሐዋርያቱ አብሮት የተጓዘው ይሁዳ አሳልፎ ሰጠው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ በመክዳቱ እጅጉን ተፀፀተ። ልብ ብሎ ላስተዋለው እውን የሰው ልጅ ለፈጠረው አምላኩ እንኳ ያልሳሳ ምን ያህል ድብቅ አውሬአዊ ባህሪ ያለውና ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ፈጻሚ መሆኑን ነው።

በዓለማችን በዘመነ ናዚ ሒትለር በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሰው ልጆችን ቋንቋ ከሚገልፀው በላይ መጫወቻ አድርጎ በገዳይነቱ ታሪክ ሆኖ ሄደል፣ የጣልያኑ ሞሶሎኒ እንዲሁ። እውን በጃፓን ሒሮሺማና ነጋሳኪ የተጣሉት የአውቶሚክ ቦንቦች ለአሜሪካን ደህንነት ሲባል በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ንጹሐን ዜጎች ሰኮንድ በማይሞላ ጊዜ ወደ አመድ መለወጥ ነበረባቸውን?

የዩጋንዳው ኢዲያ ሚን ዳዳ፣ በደል ቦካሳ (አፄ) ማዕከላዊ አፍሪካ፣ የቺሌው ፒኖቼ፣ የካምቦዲያው ፖልፖት፣ ፍራንኮስ ዱቫልየር (ሃይቲ)፣ የኢትዮጵያው መንግስቱ ኃይለማርያም እውን ከዲያቢሌስ ሳትናኤል አይመደቡምን? አልፋ ኦሜጋ ላልሆነው ሥልጣናቸው ስንቱን

አሰቃይተዋል፣ የስንቱን ደም ጠጥተዋል። ዓለም በየወቅቱ ብቅ ያሉባትን እነኚህን ገዳይ መሪዎች ስታስታውስ "ስለ ፍትህ ስለ ሰው ልጅ መብት" መሞገት ነበረባት። ግና ገና ነው። ዓለማችን ውበቷን ያጠፋው፣ የቀነሰው የሰው ዕልቂትና መከራ አለማብቃቱ ነው። ዛሬ "ዓለምን መቆጣጠር" አለብን ባዮች ኃያላን መንግስታት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የጠሉትን ለፍርድ ሲያቀርቡ አንድ ትውልድ የቀበረውን እንደ ፋሺስቱ መንግስቱ ኃይለማርያም ዓይነት ገዳይ ደግሞ ሽፋን ሰጥተውና የጭፍጨፋ ታሪኩን ሸፋፍነው ሲያስቀምጡ እውን ለሀገራችን "የፍትህ ያለ" ሞጋቹ ማነው ያሰኛል።

ዛሬም መከራው ሳያበቃ በየአካባቢው የሚደረገውን የጅምላ ጭፍጨፋ ስናይ "ምነው ኢትዮጵያ ልጆችሽ ምን በድለው ነው መከራሽ የበዛው" ያሰኛል። እናት ዓለም መቼ ነው ለልጆችሽ የምትሆኚው? ኢትዮጵያዬ ዕምባችን እኮ በዛ። አንቺ ኢትዮጵያ በልተው አልጠገቡ፣ ለብሰው አላጌጡ፣ ቤቴ፣ መመኪያዬ ብለው የተቀራመቱ የጋምቤላ ወገኖቻችን አያስለቅሱሽም? አጥፊዎችሽ ምነዋ በዙ እናት ዓለም? አቅምሽ የታለ? ክብርሽን ማን ገፈፈው ሀገሬ? የኦሮሞው፣ የአማራው በአጠቃላይ የልጆችሽ መከራ ማብቂያው መች ይሆን? ምነዋ እንቆቅልሹ አልፈታ አለ?

የአረመኔው ደርግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ታሪክ ያስመዘገበው የትውልድ ዕልቂት ከዓለም የግድያ መዝገብ፣ ማኅደር ገና በአግባቡ አልሰፈረም። ምስጢረ ግድያው ገና አልተገለጠም። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከደርግ የጥፋት ዘመን ቀይ ሽብር በቀደምትነት በርካታ የጥፋት ዘመኖችን አስተናግዳለች። በወቅቱ በአለው ሥልጣኔ የተደረጉት የሰው ልጆች ዕልቂት ተመዝግበው በመረጃ መልክ ባናገኛቸውም ዘግናኝ የጥፋት ዘመናት እንደነበሩ መገመት አያቅትም። የዮዲት ጉዲት አርባ ዓመት ዘመን ምን ጥፋት አስመዝግቦ አለፈ? የግራኝ አህመድ ወረራስ? የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት በማስጠበቅና ነፃነቷን በመጠበቅ በኩል ያደረጉት አስተዋጽዎ እንደተጠበቀ በዘመነ መሳፍንትና በዓፄዎቹ አገዛዝ ዘመን ለበትረ መንግስታቸውና ለሥልጣናቸው ደህንነት ሲባል በሰው ልጅ ላይ የተደረጉት ጭቆናና ግፎች እውን በአግባቡ ተዘግበዋልን? ሀገራችን ኢትዮጵያ በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ ያጣችው ትውልድ ከ1928ቱ የጣሊያን ወረራ ጋር በተያያዘ ነበር። በተለይ የየካቲት 12 የግፍ ጭፍጨፋ ብርቅዬ ልጆቿን ቀጥፎባታል። የዕድገት መሠረቷን አናግቷል። ቀጣይ ራዕይዋን አጨልሟል።

በኢትዮጵያችን የትውልድ መመተር ክስተቶች ታሪክና አመጣጥ ገና ብዙ ጥናት ይቀረዋል። ለእኛ ትውልድ የቅርባችን ዘመነ ጥፋት የደርግ ቀይ ሽብር ሲሆን ዛሬ እሱን ልናነሳ እንገደዳለን። የደርግን አንድ ትውልድ ጭፍጨፋ በሀገርና ልጆቿ ላይ የተደረገ ዘግናኝ ዘመን መሆኑን ለትውልድ እናሳውቃለን፣ እናስተላልፋለን። የገዳዮች ደፋርነታቸው ጥፋታቸውን አምነውና ተፀጽተው አለመማራቸው ነውና ዛሬም ይህ የሚያባንናቸውን የግድያ ታሪካቸውን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠትና ልክ እንደነበሩ ለማስቀመጥ ሲውተረተሩ ይስተዋላሉ። ዛሬ የፍትህ ሚዛኑ ለገዳይ አድልቷልና እንጠቀምበት ባዮች የደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊዎች መድረኩን መሙላት እነሱ እፍረት የላቸውምና የባህሪያቸውን እየነገሩን ነው። የቁም ሞት የሞቱትና እፍረት መሸሸጊያ ዋሻቸው የምትሆነው አብረዋቸው የሚያጨበጭቡ አድር ባይ ግለሰቦችና

ቡድኖች ናቸው። አጣጥመው በጠጡት የሙታን ደም ሲሳለቁ፣ ለዳግም ሥልጣን ሲያኮበክቡ፣ እኛ "ሰማዕት" ነን ሲሉን እየታዘብን ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» ለክርስትና እምነት ተከታዮች መልካም የፋሲካ በዓል፣ እንኳን አደረሳችሁ እንላለን። ዛሬ ይህን በዓል ስናስታውስ ደርግ በ1969 ዓ.ም. ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን ልክ የዛሬ 39 ዓመት ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ ንፁሐን ወጣቶችና ታዳጊ ሕፃናት ላይ ያደረሰውን የግፍ ግድያ በመዘከር ነው። የዓለም ሠራተኞችን ቀን ሜይ ዴይ ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ የላብ አደሩን ብሶት በግምባር ቀደምነት ለማስተጋባት በተለይ በአዲስ አበባ በየአካባቢው ሰልፍ የወጡ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የደርግ ቢአር ጥይት ተርከፈከፈ። የሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሜይ ዴይ መታሰቢያ ሰልፍ ሲጀመርና የደርግ የጥይት እሩምታ ሕፃናት ላይ ሲርከፈከፍ እኩል ሆነ። በየአካባቢው የወጣው ሰልፈኛ በጥይት ተጨፈጨፈ። ምድር በደም ታጠበች። ሕፃናት በአንድነት እንደተሰለፉ በአንድነት ተቃቅፈው ወደቁ። ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሜይ ዴይ የ"ደም" ቀን ሆነ። መብት ለላብ አደሩ የጠየቁ በደርግ ጥይት ተቆሉ። ከምሽቱ ሰልፍ በአጋጣሚ ያመለጡ ምሽቱንና ለሊቱን ከየቤታቸው እየተለቀሙ ተረሸኑ። በዚህ ምሽት አራት ልጆቻቸውን ያጡት እናት ዕድሜያቸውን ሁሉ የልጆቻቸውን ፎቶ በክብር እተሸፈነ ሳጥናቸው አስቀምጠው ያነቡታል። ዛሬ የእሳቸው ፋሲካ የልጆቻቸው ሙት ዓመት ሀዘን መታሰቢያ ነው። ይህ ማፈሪያና አንገት ሊያስደፋ የሚገባው ድርጊት ነው ዛሬ "ጀግና" ሊባልለት የሚከጀለው። አንድ ቤተሰብ አይደለም በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብ ያወደመ ፋሽስት መሪ፡ ዛሬ እንደ "ጀግናና ሀገር ወዳድ" ታሪኩን ለማደስ ሲሞከር፡ ግብረአበሮቹስ እፍረት እርቋቸዋልና ባይደንቀንም፤ ስንት አውቀናል፣ አንብበናል፣ ተምረናል፣ የፖለቲካው ተንታኝ ነን ባዮች ምን ነካቸው? እውን ፍርሃት አዶ ከብሬ እየጋለባቸው ነው? ወይስ የዛሬ 39 ዓመት "እይው ይህን አድር ባይ..." እንዳለችው ጎሕ ዛሬም አድር ባዩ አየሩን ሞላው? በ17 ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው ታሪካቸው ግድያ የሆኑትን ዛሬም በፖለቲካው ሰግስገን የነሱ አድማቂዎች ሲኮን "እውን ሀገራችን ሰው አጥታ ነውን?" ያሰኛል። ፋሺስት መንግስቱ ኃይለማርያምና የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጭዎችን ጨምሮ በመላዋ ኢትዮጵያ የድርጊቱ ተሳታፊ የነበሩ የደርግ ገዳዮች ጉዳይ ገና ፍትህ ያላገኘ፣ እንደ ባህላችንም ሆነ እምነታችን ይቅር ለሕግዚሃብሔር ያልተባለለት ጉዳይ ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ሀገራችን ለዜግነት መብት፣ ላልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት፣ ለሕዝብ መንግሥት ምሥረታ በሚደረጉ ትግሎች መታሰር፣ መሰቃየት፣ መተልተልና መገደል ፋሽስት ደርግ በጅምላ ያካሄደውን ጭፍጨፋ ነው ዘረኛው ወያኔ የቀጠለበት። ደርግ በንጹሃን ዜጎች፣ ለሀገርና ሕዝብ በቆሙ የያ ትውልድ አጥንትና ደም በሠራላቸው ድልድይ ተረማምደው ነው ወያኔና ሻቢያ ለሥልጣን የበቁት። የሀገር አለኝታዎችን ቀድሞ ቀበረላቸው። የተረፉትንም አሽመደመደላቸው። ደርግ ለወያኔና ለሻቢያ ባለውለታቸው ነውና የተቀበረ ኢሠፓና ደርግ ማቆጥቆጥ እጅጉን ሊያሳፍር ይገባል። ለዚህ ደግሞ ደርግ፣ ወያኔና ሻቢያ አንድም ሶስትም ናቸው ለማለት ወኔው የሸሸው አንድነት ኃይልም አስተዋጽዎ ቀላል አይደለም። በእኛ ማንቀላፋት እነሱ ቀና ብለዋልና። 17 ዓመት ሀገርና ሕዝብ ገድሎ

የፈረጠጠ መሪና ደርግ "የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው" እንዲሉ ፕሬዜዳንታችን እየተባለ ሲሞገስ እየታዘብን ነው። የዛሬ 39 ዓመት በአንድ ጀምበር ያፈሰሱት ደም ለማንነታቸው ከበቂ በላይ ማስረጃ ነው። 17 ዓመት የሕዝብንና ልጆቹን ደም ሲጠጣና ሲያጓራ የኖረ ደርግ ዛሬ ስለ መብትና ሀገር ለመጮህ የሞራል ብቃቱም የለው። መጀመሪያ የተሸከሙትን ወንጀል በአግባቡ ማራገፍ አለባቸው።

የዚያን ትውልድ ታሪክ ማሰባሰብና ለታሪክ ተመራማሪዎች፣ ፀሀፊዎችና ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ አንዱ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው «ያ ትውልድ ተቋም» የዛሬን ቀን በማስታወስ ለሀገራቸው ሉዓላዊነትና ለሕዝባቸው ክብር ሲሉ በተለያዩ አገዛዞች መስዋትነት ለከፈሉና እየከፈሉ ላሉ እንዲሁም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው በትውልድ መመተር ቀይ ሽብርና ነፃ እርምጃ ለወደቁት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የ«ያ ትውልድ ተቋም» ድረ ገጽ (www.yatewlid.org or www.yatewlid.com ) የዛሬ አራት ዓመት ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 29, 2012) ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማበርከታችንን እያስታወስን የጥረታችንን ቀጣይነት በድጋሚ ልንገልጽ እንወዳለን።

ደርግ ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. የመንግሥቱ ኃይለማርያም የቤት መንግሥት ግድያ በማስታከክ ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. በተለይ በኢሕአፓ ጥላ ሥር የተሰለፉ፣ የደገፉ፣ ያዩ፣ ያሰቡ፣ ያለፉትን ከሕፃናት እስከ አዛውንት ደም በማፍሰስ የበላይነቱን ለማረጋገጥ፣ ደም የተሞላ ጠርሙስ "በአብዮት" አደባባይ ከሰበረ በኋላ የቀይ ሽብር ድህረ ዝግጅት "ነፃ እርምጃ" የበርካታዎችን ሕይወት በየደቂቃው እየነጠቀ ያለፈበት ፋሽስታዊ ወቅት ነበር።

የዛሬ 39 ዓመት ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በመላዋ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዓለም አቀፍ የሠራተኞችን ቀን፣ ሜይ ዴይ ምክንያት በማድረግ አባላቱና ደጋፊዎቹ በየአካባቢያቸው በሰላማዊ ሰልፍ የተነሱበትን ዓላማ በማስተጋባት የትግል አንድነታቸውን ለመግለጽ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ለሰልፍ ተንቀሳቀሱ።

ዓለም አቀፍ የላብ አደሩን ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ከደርግ ልቅ ያጣ ጭፍጨፋ አንፃር በዕለቱ ማክበር እንደማይቻል የተገነዘበው ኢሕአፓ፣ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ሀገሩና ለጭቁን ሕዝቦች ያለውን ታማኝነትና የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ ሰላማዊ ሰልፉ የተዘጋጀው ዓርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ነበር። በሰላማዊ ሰልፍ ለማክበር የተንቀሳቀሰውን ሰልፈኛ ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያምና ጀሌዎቹ አብዮት አደባባይ በምሳሌነት ያፈሰሱትን ደም ሊጠጡ ቋምጠውና አድፍጠው ተጠባበቁ። ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች "ፍጹም ነው እምነቴ" እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በደም ታጠቡ፣ የደም ዳመና ወረደባት። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች የሽብር ለሊት ሆነ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፣ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፣ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፣ እናቶች አባቶች ሀዘን፣ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው። ልክ የዛሬ 39 ዓመት፤ ሜይ ዴይ የ"ደም" ዕለት ሆነች።

አብረን ተሰልፈን፣ አብረን ጮኸን፣ አብረን ታግለን፣ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፣ ልናስባቸው ይገባል። ደማቸውን ያፈሰሱት፣ አጥንታቸውን የከሰከሱት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!" "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም!" እየፈከሩ፣ "ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት" እየዘመሩ፣ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፡ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፣ ደማቸው ደማችን ነውና፡ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዥችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት ወስደው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይተካ ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

ዛሬ የበርካታ ክርስትና እምነት ተከታይ ቤተሰቦች የፋሲካ በዓል በሀዘንና በትካዜ የተሞላ እንደሚሆን እርግጠኞች ነን። የዛሬው ፋሲካ በዓል 39 ዓመት ወደ ኋላ ሲያስጉዘን ደርግ የሕፃናት ሥጋ የበላበት፣ ደም የጠጣበት፤ የየካቲት 12ቱ የግራዚያኒ ጭፍጨፋ በሀገር አውሬ ዳግም የሆነበትን ዘመን እያስታወስን ነው። በፋሲካ ዋዜማ ለሊት እነዚያ ሕፃናት ከእንቅልፋቸው እየተቀሰቀሱ ዶሮ ሳይሆን ጥይት ተቀለቡ። ከቤተሰቦቻቸው ጋር የጋራ ማዕድ ሳይሆን ከጓደኞቻቸው ጋር የጋራ ጉድጓድ ተላበሱ። ለክርስቲያን እምነት ተከታዮች የዛሬ ፋሲካ ባህላቸው የኢትዮጵያ ልጆች 39ነኛ የሙት ዓመት መታሰቢያቸው ሆኖ እንዘክራቸዋለን። የምንቆርሰው ዳቦ በነኚህ ሰማዕት ሕፃናት ስም ይሆናል። በዓሉን የነሱም በዓል አድርገን እናከብረዋለን። ክብር ለእናንተ፣ ምን ጊዜም አንረሳችሁም ታሪክና ትውልድ ዘላለማዊ ክብር ይሰጧችኋል እንላቸዋለን። ይህ ነው የዛሬ የፋሲካ ባህል ትዝታችን።

የዘንድሮው ሜይ ዴይ ዕለቱ ከሀገራችን የክርስትና እምነት ተከታዮች የፋሲካ በዓል ጋር በመገጣጠሙ የሜይ ዴይ ዝክረ ሰማዕታት ጽሁፋችንን ከእምነቱ ጋር ብናያይዘውም በኢሕአፓ እና በያ ትውልድ የትግል ታሪክ እስላምና፣ ክርስቲያኑን፣ እንዲሁም እምነት የለሹን ወገን በሙሉ በጋራ ያሰለፈና ሁሉም በጋራ መስዋዕትነትን የከፈሉ መሆናቸውን በመዘንጋት አይደለም። በርካታ የእስልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን በሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. እልቂት ተጨፍጭፈዋል፣ የደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰለባ ሆነዋል። ጽሁፋችን ከበዓሉ ገጠሞሽ ጋር ለማዛመድ እንጂ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችንን ሃይማኖትና ዘር እንዲሁም ቋንቋ ሳይለይ የቀጠፈ ዘመነ ጥፋት የደርግ ቀይ ሽብር መሆኑን ዳግም ልናሰምርበት እንወዳለን። የዘንድሮው ሜይ ዴይ ሃይማኖት፣ ዘርና ፆታ ሳይለይ ሁሉም የሚዘክረው የሰማዕታት ቀን ነው። ዝክረ ሰማዕታት የሜይ ዴይ ዕትማችንም ለሁሉም የኢትዮጵያ ሰማዕት ወገኖች መዘክር ይሁንልን።

የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወገኖቻችን ደም አይደርቅም!
ዛሬም ስለ ፍትህ እንጮኻለን!
«ያ ትውልድ ተቋም» ሚያዝያ 21 ቀን 2008 ዓ.ም. (May Day 2016)

ኢሜል : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
ምስለ ገጽ : yatewlid